

**ኩርኮራን ለማስተዋወቅ በEthiopian forum for poltical civility በቀረበው «ውይይት» ላይ የተሰጠ አስተያየት፤**

*በቅድሚያ አቶ ዘሪሁን ተሾመ ኩሩኮረን በእውቀትም ሆነ በድፍረት ለህትመት በማብቃታቸው ባርኔጣዬን ከእራሴ ላይ ከፍ አድርጌ ያለኝን አድናቆት ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡*

*ይህ አስተያዬት ኩርኮራን ለማስተዋወቅ በፎረሙ ላይ ከጸሀፊው ጋር የተደረገው ቃላ ምልልስና፤የመጸሀፉ ቅንጫቢ* ( exceprt ) *እንዲሁም ከጸሀፊው ጋር ባለኝ የቆየ ትውውቅ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡*

*ኩርኮራ በስፋቱም ይሁን በጥልቀቱ በኢትዩጵያ ማሕበራዊና ፖለቲከዊ ታሪክ ውስጥ አብይት ቦታ የሚሰጣቸውን እያንዳዳቸው ወፍራም ጥራዝ የሚወጣቸውን ርእሶች ያከተተ ነው፡፡ የተዋጣለት ፅሁፍ መለኪያው የጥራዙ ውፍረት ይመስል እነዚህን እራሳቸውን የቻሉ ሰፋፊ ጉዳዬች በትልቅ መወጠሪያ ሚስማር አያይዞ ያቀረበ ፅሁፍ መምሰሉ ቅር አሰኝቶኛል፡፡ሰለ መፅሀፉ የስነጹሁፋ ብቃት ( ለንባቢያን በሚገባ ቋንቋ መጻፉን በሚመለከት) እና በይዘቱ ጥልቀት ላይ መጽሀፉ እስከማነብ ድረስ ደምዳሚ አስተዬየት ከመስጠት መቆጠብ የግድ ይላል፡፡*

*በትውውቁ ቃላ ምልልስ ላይ በፎረሙ አስታናጋጆችም ሆነ በታዳሚዎቹ ለጸሀፊው የተሰጠው ለቅድስና የቀረበ የአክብሮት ክቦሽ የሚያሳስብ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ይህንን ለማለት ያስቻለኝ ፀሀፊው በራሳቸው አንደበት ይህ ያለቀለት ስራ ሳይሆን የንግግር ማነሳሽያ እንዲሆን በድፍረት የቀረበ ጅምር ነው፤ እንዳሉ እየታወቀ፤ በጉዳዩ ላይ የተከኑ ሊቅ* (authority) *ከአሁኑ ተብለው ለቀጣዩ ስራቸው መከቢያ ቅጽል እንዳያልቅብን ከለኝ ስጋት የተነሳ ነው ፡፡ ይበልጡንም ደግሞ መፅሀፉ ለንባብ በቅቶ በውስጡ ያከተታቸው ትንተናዎች ውሀ መያዝ መቻላቸው ገና ያልተፈተነ በመሆኑና፤ የማህበራዊና ፖለቲከዊ ትንተና በሌላ የመሻሪያ ትንተና የመተከት እጣው ብዙ በመሆኑ፤ እስቲ ለአምልዕኮት እንቸኩል ለማለት ነው፡፡ ወደፊትም ቢሆን ቁጭ ብለው የሰቀሉትን ቆሞ ለማውረድ ሊቸገር ይችላል ብዬ እሰጋለሁ፡፡*

የፎረሙን ታዳሚዎች እንዳላስቀይማቸው እንጂ፤ የክቦሽ እርከኑ እስከሚያልቅ ድረስ ለጽሀፊው የተደረገው የሙገሳ መዥጎድጎድ ሊቅ ሳይሆን ጣዖት የመፈጠር አዝማሚያ አለው የሚል ፍራቻ አለኝ።

የእናንተን እንጃ እንጂ እኔ ፕሮግራሙ ኩርኩራ ባነሳቸው ኮርከሪ ጉዳዮች ላይ በአብዛኛው የፀሀፊውን አስተያየት ያከተተ በመሆኑ በትንሹም ቢሆን ፈታኝ (critical) ጥያቄዎች ቀረበው የፀሀፊውም ይሁን የዕሁፉን ብቃት ይፈተሽል የሚል ከፍተኛ ጉጉት ነበረኝ። ፀሀፊውም ቢሆን በቃለ ምልልሳቸው ላይ የሀገራችን ጉዳይና በልሂቁ ሚና ላይ ያለው ችግር እንድን ነገር ገና ከጅምሩ በጥቅሉ መደገፍ ወይም በጥቅሉ በመቃወም ላይ የተመሰረተ፤ የተንሸዋረረ አመለከከት ነው ማለታቸው ይታወሳል። ይሁንና የቃለ መጠይቁ ሂዳት በአመዛኙ ለፓርቲ ጉባኤ እንደቀረበ ጽሁፍ አዳማጮቹ በማድነቂያ አሰተያየት ጀምረው በጭብጨባ የደመደሙት የደቦ ጨዋታ ይመስል ነበር።

እጅጉን አጨቃጫቂ በሆኑ የብሄረተኛነትና ሀገራዊ ጉዳዬች ላይ አንዱ ጀግና ሌላው ከሀዲ የሚለው የታወረ አመለከከት አብሮ መኖርን በመረዳትም ሆነ በማጎልበት ብዙም አውንታዊ አስተዋፅዖ እንደሌለ አስቀምጠዋል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ፀሀፊው በአብዘኛው የመቻቻል (accommodation) ትንተናቸውና የጊዜው መንግስት ለወሰዳቸውና እየወሰዳቸው ላሉ እርምጃዎች ፅንሰ ሀሳባዊ መሰረት ለማስቀመጥ የሞከሩ ይመስላል። ሆኖም ይህ ጥረት መንግስትን በሚውስዳቸው ከታሪክም ሆነ ከብሔራዊ ጥቅም ጋር ሚፃረሩ ውሳኔዎች ላይ ፤ ከተጠያቂነት ነፃ ለማድረግ የመሟገትን ዝንባሌ ያዘለ ትንተና ነው የሚል ጥርጣሬን ያስከትላል።

ይህ ደግሞ ከፀሀፊው ስነልቦና ፅኑነትና በራሳቸው የመተማመን ቸግርን ለመሸፋፈን ለተግባራቸው ቅቡልነት (justification) ለመስጠት የተደረገ የብልጣ ብልጦች አደናጋሪ ትነተና ነው የሚል ጥርጣሬ አለኝ። በነገራችን ላይ አቶ ዘሪሁን ተሾመን ባለፉት 20 አመታት ውስጥ ያለፉበትን የህይወት ስሜታዊ አቀበትና ቁልቁለት ጎዳና (roller coster) በቅርብ የማውቀው በመሆኑ ይህ ሙከራቸው እንደ ዱብ እዳ የሚገጥመኝ ጉዳይ አይደለም። በተለይም ፀሀፊው ያሳለፉት ውስጣዊ ረብሻ እና ውጭያዊ ፈተና በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላለው ውስብስብ

የስዕብእና ችግር አዲስ (orginial) መፍትሄ የማቅረብ እድሉ ከማንም በላይ እያላቸው፤ከህሊናቸው ጋር መታረቅ ሰላልፈለጉ ብቻ፤ በዚህ ተልከሻ መስል ጹሁፍ ቀሪውን ህወታቸውን በህሊና ባርነት ለመጨረስ የተዘጋጁ የሚመሰል አዝማሚያ በማሳየታቸው እጅጉን አዝኛለሁ::

በኢትዩጵያ የቅርብ ታሪክ ላይ በሰጡት ማህበራዊና ፖለቲከዊ ትንተናቸው፤ ፀሀፊው በአሳዛኝ ሁኔታ ስለ ዜጎች የግለሰብ ይሁን የቡድን ነፃነት ከማውሳት ተቆጥበዋል:: የጊዜውን የፖለቲከ አደረጃጀት (status-quo) ከመቀበልና ለእሱም እንድንገዛ የተወሻሸለ የመቻቻያ ፅንስ ሀሳብ ንድፍ ከመስበክ ልይቅ፤ ለሀገራችን የማህበራዊና ፖለቲከዊ ችግር መንስዔውም ይሁን መፍትሄው በዜጎች መብት መከበር ዙሪያ ያጠነጠነ ሆኖ ሳለ፤ ይህ ጥያቄ እምብዛም ስለማይመቻቸው ወይንም ከህልውናቸው መሰረት ከሆነው የጎሽ ጎሽ አበጀህ ፖለቲከ ጋር ስለሚጋጭ ይመስላል፤ ይህንን መሰረታዊ ጉዳይ ሊያነሱትም አልሞከሩም::

ሌላው በፕሮግራሙ በስተመጨረሻ ለተጠየቁት ከኢህአደግ መንግስት ጋር ስላላቸው ፀብና ወዳጅነት ጥያቄ የሰጡት «ቂም ለማንም የማይበጅ በሽታ» መሆኑን ያመላከተው ዲፕሎማሲያዊ መልሳቸው ነው:: እዚህ ላይ ጥሩ ብለዋል ፤ቂም ሊቀር የሚገባው የዝምድናና የመቀራረብ ደነቃራ መሆኑ እምብዛም አያከራክርም ፤ነገር ግን አብሮ መኖርና መቻቻልን ለማጎልበት መርህ እና ተአማአኒነት ( credibility) በግድ መከፈል ያለበት ዋጋ አይመስለኝም:: በጊዜው ለተነሳው ገዥ የሚስማማ ቅኝት መጫወት አስከተቻለ ድረስ ታአማአኒነት ብዙም እንቅልፍ የሚነሳኝ ነገር አይደለም ከላሉኝ በስተቀር፤የጊዜን ፈተና የማያልፍ አቋምም ይሁን ተግባር በየግዜው በሚቀርብለት ፈተና መንገዳገዱና በመጨረሻም በአፍጢሙ መደፋቱ ስለማይቀር፤ ለመርህ መገዛቱን የበለጠ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል እላለሁኝ::

በመደምደሚያም ኩርኮራ ለንባብ በቅቶ በጥልቅ አንብቤና መርምሬ የጠለቀ አስተያዬት አስከማቀርብ ድረስ ቸር ይግጠመን::

**የናንተው ልጅ አምሀ ዘውዴ ነኝ**
**ጁላይ 2007**